STAY SAFE MN

# የኮቪድ-19 ክትባቶች እና እርግዝና

## የኮቪድ-19 ክትባት ለነፍሰ ጡር ሰዎች ይመከራል



- ነፍሰ ጡር ሰዎች ነፍሰ ጡር ካልሆኑ ሰዎች ይልቅ ለከባድ የኮቪድ-19 በሽታ ተጋላጭነታቸው ከፍ ያለ መሆኑን እናውቃለን።
- በእርግዝና ወቅት ስለሚሰጥ የኮቪድ-19 ክትባት ደህንነት እና ክትባቱ በነፍሰ ጡር ሰዎች ላይ እንዴት እንደሚሰራ ያለን መረጃ እያደገ ነው።
- የእርግዝና ውጤቶች በክትባቱ አይጎዱም። ይህም ህጻኑን የሚነኩ ውጤቶችን ያጠቃልላል። መረጃው በእርግዝና ወቅት የኮቪድ-19 ክትባትን የመከተብ ጥቅሞች ከሚታወቁት ወይም ሊከሰቱ ከሚችሉ የክትባት አደጋዎች እንደሚበልጡ ይደግፋል።
- ነፍሰ ጡር ከሆኑ፣ ከኮቪድ-19 ከባድ በሽታ ለመጠበቅ እንዲረዳዎ ክትባቱን ይውሰዱ።
- ጥያቄዎች ካሉዎት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።

## ወደፊት ልጅ መውለድ የሚፈልጉ ሰዎች የኮቪድ-19 ክትባትን መውሰድ ይችላሉ።

- አሁን ለማርገዝ እየሞከሩ ከሆነ ወይም ወደፊት ለማርገዝ ፍላጎት ካለዎት የኮቪድ-19 ክትባት እንዲወስዱ ይመከራል።
- የመራባት ችግሮች የማንኛውም የኮቪድ-19 ክትባት የጎንዮሽ ጉዳት ስለመሆኑ ምንም ማረጋገጫ የለም።

MINNESOTA

**mn.gov/vaccine**

Minnesota Department of Health | health.mn.gov | 651-201-5000 | 625 Robert Street North PO Box 64975, St. Paul, MN 55164-0975
ለመጠየቅ health.communications@state.mn.us ን ያነጋግሩ። (Amharic)

10/15/2021